# የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛ ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው ሪፖርቶች መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ

ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

**ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣**

የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ወጪ፣**

1. ኤጀንሲው ለተገለገለበት የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያ ከየሐ ሪል እስቴት በቀረበው ማስረጃ መሰረት ብር 7701.41 መከፈል ሲገባው ብር 18,039.30 ተከፍሎ በወጪ ተይዞ በመገኘቱ ብር 10,337.89 ማስረጃ ሳይቀርብለት በብልጫ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ ::

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

2. በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ሳይወራረድ የተገኘ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 73,992.34 መገኘቱ::

**በጀት፤**

3. ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ ብር 170,782.20 መገኘቱ፤

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ከተገለፁት ሁኔታዎች በስተቀር በእኛ አስተያየት የኤጀንሲው የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣**

4. ያልተሰራበት በጀት ብር 8,076,085.60 መገኘቱን፤
5. በበጀት ዓመቱ የክፍያ ጣሪያ ወይም ተመን ሳይወጣለት ለተለያዩ የተንቀሳቃሽ እና የቀጥታ መስመር ስልኮች ያለገደብ የፍጆታ ክፍያ በድምሩ ብር 74,902.75 ወጪ ሆኖ መገኘቱ::

**ሌሎች ጉዳዮች፤**

**ንብረት**

6. በብር 402,107.00 የተገዛ ጀኔሬተር ያለ አገልግሎት ለ6 ዓመታት በመጋዘን ውስጥ ተቀምጦ የቆየ መሆኑ::
7. የሰሌዳ ቁጥሩ 4-03194-ኢት የሆነ ላነድ ክሩዘር እና የሰሌዳ ቁጥር 30-054 ሾርት ቤዝ ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ ቆመው ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ ::

ከሠላምታ ጋር

-----------------------

ሚኪያስ ተራዳ
ኦዲት ሥራ አስኪያጅ